# ዮሴፍና ገጠመኞቹ

# The Adventures of Joseph

ይህን መጽሐፍ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ አሳታሚው ወይም ያለ ተርጉሚው ፈቃድ ማባዛት የተከለከለ ነው።

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RP TR 20

# ዮሴፍና ገጠመኞቹ

ትርጉም ፡- ራዕይ አሳታሚ

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 1997 ዓ.ም.

## ልጆች ይህን መጽሐፍ እናስተዋውቃችሁ

ድሮ፣ ድሮ፣ ዮሴፍ የተባለ ልጅ ነበር:: ታሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለይ ኦሪት ዘፍጥረት በሚባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከምዕራፍ 37 እስከ ምዕራፍ 47 ይገኛል::

ዮሴፍ ልዩ ጠባይ ነበረው:: የእርሱ ጠባይ ከሌሎች ልጆች ይለያል:: አስገራሚ ነገሮች ይታዩበት ነበር:: ብዙ ችግር ደርሶበታል:: በችግሩ ሁሉ እግዚአብሔር አብሮት ነበር:: ከችግሮቹ ሁሉ እንዴት እንደወጣም በዚህ መጽሐፍ ተጽፏል::

መንፈሳዊ ታሪኮች ለልጆች ይጠቅማሉ:: የዮሴፍ ታሪክ በብዙ የአለም ቋንቋዎች ተጽፏል:: ብዙ ልጆች አንብበውታል እናንተም እንድታነቡት በቀላሉ ተዘጋጅቶ ይሄው ቀርቦላችኋል:: በሉ ቀጥላችሁ ይህን መጽሐፍ አንብቡ:: ብዙ ትምህርት ታገኙበታላችሁ:: ለዚህ እግዚአብሔር ይርዳችሁ::





# የዮሴፍ ታሪክ

በድሮ ጊዜ ከነዓን በሚባል አገር
ዛሬ ደግሞ እስራኤል በተባለ አገር
ያዕቆብ የሚባል ሰው ይኖር ነበር::
ያዕቆብ ብዙ ልጆች ነበሩት::
ከልጆቹም አንደኛው ዮሴፍ ይባል ነበር::

የዮሴፍ ወንድሞች እረኞች ነበሩ::
የአባታቸውን በጎችና ፍየሎች ይጠብቁ ነበር::
በቂ ሣርና ውሃ ባለበት ሥፍራ ያስማሯቸው ነበር::

## የዮሴፍ ጥብቆ

ያዕቆብ ባረጀ ጊዜ ዮሴፍን ወለደ::
በእርጅናው ጊዜ ስላገኘው ወደደው::
ስለዚህ ያማረ ጥብቆ አሰፍቶለት ነበር::



የዮሴፍ ወንድሞች አባታቸው
ዮሴፍን ከነሱ አብልጦ እንደወደደ አዩ::
ስለዚህ ዮሴፍን ጠሉት::

ከጥላቻቸው የተነሣ ሊያዩት አይፈልጉም ነበር::

በደህና ሁኔታም አያነጋግሩትም ነበር::


## አስገራሚው ሕልም

አንድ ሌሊት ዮሴፍ እንደተኛ ሕልም አየ::
ያየውንም ሕልም ለወንድሞቹ ነገራቸው::
ወንድሞቹም ሕልሙን ሲሰሙ ተቆጡት::

ዮሴፍ የነገራቸው ሕልም እንዲህ ነበር::

ሁላችን በእርሻ ማሣ ውስጥ ነበርን
የስንዴ ነዶ እናስር ነበር
የእኔ ነዶ ቀጥ ብላ ቆማ ሳለች
የእናንተ ነዶዎች በእኔ ነዶ ዙሪያ ተሰበበሰቡ::
ከዚያም ለእኔ ነዶ ሰገዱ አላቸው::





ወንድሞቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ተቆጡ::
የእኛ ንጉሥ ልትሆን ፈለክ እንዴ! አሉት::
በዚህ ምክንያትም በጣም ጠሉት::

ዮሴፍ ቀጥሎ ሌላ ሕልም አለመና
እንዲህ ብሎ ነገራቸው

በሕልሜ ፀሐይና ጨረቃ አየሁ
አሥራ አንድ ክዋክብትም ነበሩ
ሁሉም በፊቴ ለገዱ አላቸው::



ይህንንማ ሲሰሙ እንቀው ሊገድሉት ፈለጉ::

ዮሴፍ ይህንኑ ሕልሙን ለአባቱም ነገረው::
አባቱም ሲሰማ ተቆጣ::
ምን ዓይነት ሕልም ነው?
እኔ እናትህና ወንድሞችህ ሁላችንም
ወድቀን ልንሰግድልህ ነው? አለው::
ያዕቆብም ሕልሙን እያሰላሰለ
ሲፈጸም ለማየት በትዕግስት ጠበቀ::

## የዮሴፍ ወደ ወንድሞቹ መላክ

አንድ ቀን የዮሴፍ ወንድሞች
በጎቻቸውንና ፍየሎቻቸውን ይዘው
በቂ ሣርና ውሃ ወዳለበት
ለኬም ወደተባለ ስፍራ ሄዱ::
ስለዚህ ያዕቆብ ዮሴፍን
ወንድሞችህ ከብቶቻቸውን ይዘው
ወደ ሴኬም ሄደዋል



ኸረ እባክህን እንዴት እነደለነበቱ
ሂደህ እያቸውና መጥተህ ንገረኝ ብሎ
የሚበሉትን ምግብ አሲዞ ላከው::
ዮሴፍም ደህና መሆናቸውን ሊያይ
መጥቶም ለአባቱ ሊነግረው
ምግብ ተሸክሞ ዱላውን በእጁ ይዞ
በኬብሮን ሸለቆ በኩል ተጉዞ ሴኬም ደረሰ::





ዮሴፍ ሴኬም ከደረሰ በኋላ
ወንድሞቹን አላገኘም::
ከዚያም ወንድሞቹ የሄዱበትን ሲያፈላልግ
አንድ ሰው አገኘ::
ሰውዬውም ዮሴፍን ምን ትፈልጋለህ? አለው::
ዮሴፍም ወንድሞቼ በጎችና ፍየሎች ይዘው
ሣርና ውሃ ፍለጋ ወደዚህ መጥተው ነበር
አሁን ላገኛቸው አልቻልሁም
እባክህ አይተሃቸው ከሆነ ንገረኝ አለው::
ሰውዬውም ሰሞኑን እዚህ ነበሩ
በኋላ ግን ወደ ዳታን እንሂድ ሲሉ
ሰምቻለሁ አለው::
ዮሴፍም ሰውዬውን አመስግኖ
ወንድሞቹን ፍለጋ ወደ ዳታን ሄደ::





ወንድሞቹም ዮሴፍ ሲመጣ አይተው
ያ ባለ ሕልሙ መጣ ተባባሉ::
ሊገድሉትም ተነጋገሩ::
ገድለን ጉድጓድ ውስጥ እንጣለውና
ብንጠየቅ አውሬ በላው እንላለን
በዚህም የሕልሞቹ መጨረሻ ይሆናል ተባባሉ::
ሮቤልም ይህን በሰማ ጊዜ
ዮሴፍን ሊያድን አሰበና
አንግደለው በጉድጎድ ውስጥ እንጣለው አለ::
ይህን ማለቱ ደብቆ



አባቱ ዘንድ ሊወስደውና
ከሞት ሊያድነው ፈልጎ ነበር፡፡
ዮሴፍም ወንድሞቹ ዘንድ በደረሰ ጊዜ
ይዘው እየገፈተሩ ጥብቆውን ቀደዱበት፡፡
ከዚያም ጉድጓድ ውስጥ ወርውረው ጣሉት፡፡



ዮሴፍ የተጣለበት ጉድጓድ
ውሃ ያልነበረው ደረቅ ቦታ ነበር፡፡
ወንድሞቹ ጉድጎድ ውስጥ ከጣሉት በኋላ



ተሰብስበው ምሣቸውን ይበሉ ጀመር፡፡

## ዮሴፍ ለባርነት መሸጡ

ወንድማማቾቹ ተሰብስበው ምሳቸውን እየበሉ ሳሉ
ነጋዴዎች ባጠገባቸው ሲያልፉ ሲመጡ አዩ፡፡
ነጋዴዎቹ የእስማኤል ሰዎች ነበሩ፡፡
ብዙ ዕቃ ግመሎቻቸው ላይ ጭነዋል፡፡

ነጋዴዎቹም ከገለዓድ ከተማ የመጡ ነበሩ፡፡
ብዙ ዕቃዎችን ገዝተው የሚሸጡ ናቸው፡፡
በግመሎቻቸው ላይ ጥሩ ቅመሞችንም ጭነዋል፡፡
ይሁዳ ባያቸው ጊዜ እንዲህ አለ፡፡
ዮሴፍ ወንድማችን ስለሆነ ልንጎዳው አይገባም
ለነዚህ ነጋዴዎች ብንሸጠው ይሻላል አላቸው፡፡
ይህን በመነጋገር ላይ ሳሉ
ነጋዴዎቹ እነርሱ ዘንድ ደረሱ፡፡
ከምድያውያን አገር የመጡ ነበሩ፡፡
ነጋዴዎቹ እነርሱ ዘንድ ሲደርሱ
ወንድሞቹ ዮሴፍን ከጓድጓድ ውስጥ አወጡትና
በሃያ ብር ለነጋዴዎቹ ሸጡት፡፡



ነጋዴዎቹም ዮሴፍን ይዘው ወደ ግብፅ ሄዱ::


ሮቤል መጥቶ ጉድጓድ ውስጥ ቢመለከት
ዮሴፍን ጉድጓድ ውስጥ አላገኘውም::
ይህኔ በጣም ስላዘነ አለቀሰ::
ኋላም ለወንድሞቹ እንዲህ አላቸው
ኧረ ዮሴፍ በጉድጓድ ውስጥ የለም
ምን ወስደው ይሆን? አዬዬ ወዮልን አለ::

## ትልቁ ውሸት

የዮሴፍ ወንድሞች ፍየል ካረዱ በኋላ
የዮሴፍን ጥብቆ በደሙ ውስጥ ነከሩ::
ከዚያም ጥብቆውን ወደ አባታቸው ዘንድ ወስደው
ይህን ጥብቆ በጥንቃቄ ተመልከተው::
በመንገድ ላይ ወድቆ አገኘነው
የልጅህ የዮሴፍ ጥብቆ ነውን? አሉት::
ያዕቆብም ጥብቆውን ደህና አድርጎ ተመለከተ::
የልጁ ጥብቆ መሆኑንም አወቀ::



በእርግጥ የልጄ ጥብቆ ነው::
ልጄን አውሬ በልቶታል አለ::
ዮሴፍንም በጣም ይወደው ስለነበር
ልብሱን ቀደደ በጣም አድርጎም አለቀሰ፣ አዘነ::




በጣም ስላዘነም ለብዙ ጊዜ አለቀሰ::
ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ ሊያጽናኑት ሞከሩ::
ያዕቆብ ግን ሊጽናና አልቻለም::
ተውኝ ልጄን አጥቻለሁ አላቸው::
የምወደው ልጄ ዮሴፍ እንደ ሞተ
እኔም መሞቴ አይቀርም አላቸው::



እርሱ ወዳሰበት እስክሄድ ድረስ
ለምወደው ልጄ እለቅሳለሁ አለ::
ለቅሶውንም ቀጠለ::


## ዮሴፍ በማያውቀው አገር

ነጋዴዎቹ ዮሴፍን ይዘው ግብፅ እንደ ደረሱ
ለጵጥፋራ ሸጡት::
ጵጥፋራ ፈርዖንን የሚጠብቁ ወታደሮች አዛዥ ነበር





ዮሴፍ በጵጥፋራ ቤት ባሪያ ሆኖ ሲኖር
የጵጥፋራ ሚስት ወደደችውና የማይገባ
ነገር እንዲያደርግ ጠየቀችው::
የጵጥፋራ ሚስት የጠየቀችው
ዝሙት እንዲፈጽም ነበር::
ዮሴፍ ግን እንዲህ ያለ ነገር አላደርግም አላት::
ከዚያም በውሸት ከሰሰችው::
ዮሴፍ ያለ ጥፋቱ እስር ቤት ገባ::
እርሱም በእስር ቤት ሳለ
ከርሱ ጋር የታሰሩ
ሁለት የፈርኦን ሠራተኞች ነበሩ::
እነርሱ ህልም አዩ::
ህልማቸውንም ዮሴፍ ፈታላቸው::
ዮሴፍ ይህን ሕልም ከፈታ በኋላ
ሁለት ዓመት አለፈ::
አንድ ቀን ደግሞ ፈርዖን ሕልም አየ::
ሰው ሁሉ ሕልሙን ሊፈታለት አልቻለም::



ታዲያ ዮሴፍ ሕልም እንደሚፈታ ንጉሡ ሰማ::
ከዚያም ዮሴፍን ከእስር ቤት አስጠራውና
ህልሙን ነገረው ሕልሙን በሙሉ ፈታለት::

የሕልሙም ትርጉም እንዲህ የሚል ነበር
ሰባት ዓመት ጥጋብ ይሆናል ቀጥሎም
ሰባት ዓመት ደግሞ ረሃብ ይሆናል::

ስለዚህ በሰባቱ የጥጋብ አመት
ብዙ እህል በጎተራ ክተት::
ሰባቱ የረሃብ አመት ሲመጣ
በጎተራ ያለውን ምግብ እያወጣህ
ለህዝቡ አድል አለው::

ፈርዖንም በዮሴፍ የሕልም ፍቺ ተደሰተ::
ዮሴፍም ከእርሱ በታች ሆኖ
በጥጋቡ ዘመን ምግብ
በጎተራ እንዲገባ እንዲያደርግና
ግብፅን እንዲገዛ ሾማው::





## ዮሴፍ የግብፅ አገር ገዥ ሆነ

ዮሴፍ አዋቂ ሰው ነበር::
ለፈርዖን ብልህ አስተዳዳሪ ሆነለት::
ዕድሜውም ሠላሣ ዓመት ነበር::
ከቤተ መንግስት ውጭ
በግብፅ ውስጥ ለስራ ይዘዋወር ነበር::
ልክ እርሱ እንዳለው ተፈፀመ::
ለሰባት ዓመት መከር በዛ::
ምድርም በለፊው እህል ለጠች::
ዮሴፍም ብዙ ጎተራዎች አሠራ::



እህሉንም በጎተራዎች አከማቸ::

ዮሴፍ ያከማቸው እህል ብዙ ነበር፡
ሆኖም ረሃብ ገና አልመጣም ነበር
በዚህን ጊዜ የዮሴፍ ሚስት
ሁለት ልጆች ወለደች::
ሁለቱም ወንዶች ነበሩ::

የመጀመሪያ ልጁን ስም ምናሴ አለው
ትርጉሙም "አስረሳኸኝ" ማለት ነው::
ችግሩን ስላስረሳው በዚህ ስም ጠራው::
ሁለተኛውን ልጁን ኤፍሬም አለው::
ትርጉሙ በመከራ አገር ልጅ ማግኘቱን ይገልፃል::

## ክፉው ህልም እውን ሆነ

ታዲያ ሰባቱ የጥጋብ ዓመቶች አለፉ::
የጥጋብ ዓመቶቹ የደስታ ነበሩ::
ከዚያም የረሃብ ዓመቶች መጡ::



ሰዎች የነበራቸውን እህል ጨርሰው ተቸገሩ::
ወደ ፈርዖን መጡና እህል ስጠን አሉት::
ፈርዖንም እህል የሚሰጣችሁ ዮሴፍ ነው
እርሱ ዘንድ ሂዱ
የሚነግራችሁን አድምጡ
ከዚያም ፈጽሙ አላቸው::
ረሃብ መስፋፋት ሲጀምር
ብዙ ሺህ ሰዎች እህል ለመሸመት
ዮሴፍ ዘንድ መጡ::
ከየከተሞችና ካገር ቤት መጡ::
ከአካባቢው አገሮችም መጡ::
ለእነርሱም እህል ሸጠላቸው::

## በግብፅ እህል መኖሩ ተሰማ

በከነዓንም ረሃብ ስለነበር
ስለዚህ ሕዝብ ተቸገረ:: ይህን ጊዜ ያዕቆብ
እህል የት ይገኛል ብሎ ጠየቀ::
ብዙ እህል ግብፅ መኖሩን ሰማ::

ዮሴፍ ወንድሞቹን ባየ ጊዜ
እነርሱ መሆናቸውን አወቀ::
እነርሱ ግን አላወቁትም ነበር::
እርሱም ሊታወቅ አልፈለገም::
እንዳያቸውም ቆጣ ብሎ
ከዬት መጣችሁ? አላቸው::
እነርሱም ከከነዓን መጣን አሉት::
ይህኔ የቀድሞውን ሕልሙን አስታወሰ::

ለምን መጣችሁ አላቸው?
ጌታው ሆይ እህል ልንገዛ መጣን አሉት::
እህል ልትገዙ አልመጣችሁም
እናንተ ሰላዮች ናችሁ
ልትሰልሉ መጥታችኋል አላቸው::
እኛ ንጹሐን ወንድማማቾች ነን::
የመጣነውም እህል ለመሸመት ነው አሉት::
እርሱም መልሶ ሰላዮች ናችሁ አላቸው::
እኛ አሥራ ሁለት ወንድማማቾች ነበርን::
የተወለድነውም ከአንድ አባት ነው::



አባታችንም በከነዓን ይኖራል::
አንዱ ወንድማችን ሙቶአል::
አንድ ታናሽ ወንድማችን በቤት ቀርቷል አሉት::

## ለሦስት ቀናት በእሥር ቤት

ዮሴፍም የምትሉትን አላምንም::
በእርግጥ ሰላዮች ናችሁ::
እውነታችሁን ከሆነ ታናሽ ወንድማችሁን ስታመጡ
ያኔ እውነተኞች መሆናችሁን አረጋግጣለሁ::
በሰላምም ወደ አገራችሁ ትመለሳላችሁ::
ስለዚህ አንዱ ከእናንተ ሄዶ ታናሹን
ወንድማችሁን ያምጣ::
ይህ ሲሆን አምናችኋለሁ::
ባይሆን ግን ሰላዮች መሆናችሁ ይረጋገጣል::
እስከዚያ ሌሎቻችሁ በእስር ትቆያላችሁ::
አለና ለሦስት ቀን እስር ቤት አስገባቸው::





## ታላቅ ፈተና

በሦስተኛው ቀን ወደ እስር ቤት ሄዶ
የማዛችሁን ሁሉ አድርጉ::
ካደረጋችሁ አትገደሉም::
አንዱን ወንድማችሁን ተውትና
ሌሎቻችሁ እህል ይዛችሁ ሂዱ::
አገራችሁም ስትደርሱ ታናሻችሁን አምጡ::
ያኔ እውነተኛነታችሁን አረጋግጣለሁ
እናንተም አትገደሉም አላቸው::
እነርሱም ዮሴፍ ያላቸውን ሁሉ አደረጉ::

## እርስ በርስ ተወቃቀሱ

እንዲህ ተባባሉ
በዮሴፍ ላይ ክፉ ነገር አድርገናል::
ጉድጓድ ውስጥ ለምን ጣልነው?
የሰራነው ግፍ እየደረሰብን ነው
የችግራችን ምክንያት ይህ ነው አሉ::



ሮቤልም መልሶ ተው ብያችሁ ነበር::
ግን የነገርኩዋችሁን አልሰማችሁም::
ለእርሱ ሞት ተጠያቂዎች ናችሁ አላቸው::
ዮሴፍም የሚሉትን ይሰማ ነበር::
እነርሱ ግን እንደሚሰማቸው አያውቁም ነበር::
ዮሴፍ የሚሉትን በሰማ ጊዜ
ዞር ብሎ አለቀሰና
እንባው ሲቆም ተመልሶ መጣ::
ስምዖንንም ወስዶ አሰረው::

## አስደንጋጩ ነገር

ዮሴፍ አገልጋዮቹን እንዲህ ብሎ አዘዘ::
በስልቻዎቻቸው እህል ሙሉና
በላዩ ላይ ገንዘባቸውን አስቀምጡ::
ለስንቅም የሚሆን እህል ስጡዋቸው አለ::
አገልጋዮቹም እንደታዘዙት አደረጉ::

ከዚህ በኋላ ወንድማማቾቹ
እህላቸውን ጭነው ጉዞ ቀጠሉ::
በመሸባቸውም ጊዜ መንገድ ላይ አረፉ::
ከመካከላቸውም አንዱ ለአህያው ጥሬ ሊሰጥ
ስልቻውን ፈታ ሲያደርግ
ገንዘብ ከላይ ተደርጎበት አየ::
እርሱም ባየ ጊዜ ደንግጦ ጮኸ::
ለወንድሞቹም ይኸውላችሁ የሆነ ለው
ገንዘቤን መልሶ ስልቻዬ ውስጥ ከቶታል አለ::





ይህኔ ሁሉም ጠርጥረው ስልቻቸውን ፈቱ::
የእነርሱም ገንዘብ ተቀምጦ አገኙት::
ኋላም እግዚአብሔር ምን ፈፀደብን? ተባባሉ::

ከዚያም ተጉዘው ከነዓን በደረሱ ጊዜ
አባታቸው ዘንድ ቀረቡና
የደረሰባቸውን ነገር ዘርዝረው ነገሩት::
እንዲህም አሉት::
ወደ ገዥው ስንቀርብ ተቆጣንና
ሰላዮች ናችሁ አለን::
በሚያስፈሩ ቃላትም ተናገረን::
እኛ ግን በትህትና መልሰንለት
ጨዋ ሰዎች ነን አልነው::
ሰላዮች አለመሆናችንንም አረጋገጥንለት::
አሥራ ሁለት ወንድማማቾች ስንሆን
የአንድ አባት ልጆች ነን አልነው::
አንዱ ወንድማችን እንደሞተ
ታናሹ ከአንተ ጋር መሆኑንም ነገርነው አሉት::
ሁላችንን ሊያስረን ፈለገ:: በኋላም እንዲህ አለን::
አንዱ ወንድማችሁ ታስሮ ይቆይ::



ሌሎቻችሁ እህል ይዛችሁ ሂዱ::
ስትመለሱም ታናሻችሁን ወንድማችሁን አምጡ::
ይህ ከሆነ አምናችኋለሁ::
እናንተም ምንም አትሆኑም::
የፈለጋችሁትን ያህል እህል
ገዝታችሁ ትሄዳላችሁ አለን አሉት::
ያዕቆብም ያሉትን በደንብ አደመጠ::

በጉዞ ላይ ሳሉ በስልቻዎቻቸው ውስጥ
ስላገኙት ገንዘብም ለአባታቸው ነገሩት::
አባታቸውም ሲሰማ በጣም ደነገጠ::
ዮሴፍ ሙቶአል::
ስምዖንም እዚያ ቀርቷል::
አሁን ብንያምን ልትወስዱብኝ ነው::
ባዶ እጄን ልታስቀሩኝ ትፈልጋላችሁ::
የተደራረበ ጉዳት ሲደርስብኝ ነው::
ከቶ ምን ይሻለኛል?
ሲል እያዘነ ተናገረ::





ሮቤልም አባቱ ሲጨነቅ አይቶ
አትስጋ ብንያምን መልሼ አመጣልሃለሁ አለው::
ከዋሸሁ ሁለቱን ልጆቼን ግደል::
እመነኝ መልሼ አመጣዋለሁ አለው::
ያዕቆብም መልሶ እንዲህ አለ::
ወንድሙ ዮሴፍ ሞቶአል::
ለራሔል የመጨረሻ ልጅዋ ነበር::
እኔም እንደምታዩኝ ሽምግያለሁ::
ብንያም ቢጎዳብኝ ኀዘን ያጎሳቁለኛል::
በፍጹም አልልከውም አለ::



## ብንያም መሄዱ አልቀረም

በከነዓን አገር ረሃቡ እየባሰ ሄደ::
የመጣውም እህል እያለቀ መሆኑን
ያዕቆብና ቤተሰቡ ተረዱ::
ይህን ጊዜ ያዕቆብ ልጆቹን ጠራ::
ሁሉም ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ
ልጆቼ ያመጣችሁት እህል እያለቀ ነው::
እንደ ገና ወደ ግብፅ ሂዳችሁ
እህል ገዝታችሁ ተመለሱ አላቸው::
ይሁዳም አባዬ ያልከው መልካም ነበር::
የግብፁ ገዥ እኮ ብንያምን አምጡ ብሎናል::
ይዘነው ካልሄድን አይቀበለንም::
ሳትይዙት እንዳትመጡ ብሎናል::
ሰውዬው ኃይለኛ ሰው ነው::
ይህን ባናደርግ እንቸገራለን
ስምያንንም አይሰጠንም::



ስለዚህ ብንያምን ከላከው እንሄዳለን::
ያልከውን እህልም እናመጣለን::
ያለበለዚያ መሄዳችን ምን ይጠቅማል?
ብንያምን አምጡ ብሎ አዞናል::
ሳንይዘው እንዳንመለስ አስጠንቅቆናል አለው::


ያዕቆብም ነገሩን አዳመጠና
ለምን ታስቸግሩኛላችሁ? አለ::
ይሁዳም ሰውዬው የዋዛ አይደለም::
እንዲያውም ስለቤተሰባችንም ጠይቆን ነበር::
በተለይ ስለአንተ ጤንነት ሲጠይቀኝ
ለመሆኑ በሕይወት አለ? ብሎ አለ::
እኛም ደህና መሆንህን ነገርነው::
ከዚያም ሌላ ወንድምስ የላችሁም? አለ::
እኛም አለን ብለን መለስን::
እኛ ብንያምን አምጡ ይላል
ብለን አልጠረጠርንም ነበር አሉ::

## ይሁዳ ቃል ኪዳን ገባ

ከዚህ በኋላ ይሁዳ ለአባቱ

ልጅህን ከእኛ ጋር ላከው:: ከቶ አትስጋ::
በዚህ ምክንያት እኛም በረሃብ እንሙት::
እንዳዘዝኸን ሁላችንም ወደ ግብፅ እንሂድ::
እህልም ጭነን እናምጣ አለው::
ስምዖንንም ይዘን እንመጣለን::
እመነኝ አባዬ ብንያም ምንም አይሆንም::
ለሚደርስበት ነገር እኔ ሃላፊ እሆናለሁ::
ግድ የለህም በለላም እመልለዋለሁ::
እኔ መልሼ አመጣዋለሁና አትስጋ::
ብንያምን መልሼ ባላመጣው ለዘላለም
በደለኛ ልሁን አለው::





ቀጠለና አሁንም ቢሆን ዘግይተናል::
እስከ ዛሬ ሁለት ጊዜ በተመላለስን ነበር::
ይሁን መቼም የሆነው ሆኖአል አለ::

## ለገዥው ገፀ በረከት ወሰዱለት

ያዕቆብ ሁሉንም ዝም ብሎ አድምጦ
በሉ ለሁሉም መሄዳችሁ አልቀረም::
ስትሄዱ ባዶአችሁን አትሄዱ::



ለሹሙ ጥሩ ነገሮችን ወሰዱለት::
ምርጥ ፍራፍሬዎችን በከረጢት አድርጉ::
ማርና ቅመማቅመሞችንም ጨምሩበት::
ብዙ ገንዘብም ለሸመታ ያዙ::

ብዙ ገንዘብ መያዝ ይጠቅማል
በርካታ እህል ልትሸምቱ ትችላላችሁ::
ያኔ ከዚያ ስትመጡ ሳላችሁ
በስልቻዎቻችሁ ውስጥ ያገኛችሁትንም ገንዘብ
መልሳችሁ ውሰዱና ለሹሙ ስጡ::
ሰው በስህተት በስልቻዎቻችሁ ከቶት ይሆናል::

እንዳላችሁት ብንያምን ይዛችሁ ሂዱ::
ስምዖንንና ብንያምን እንዲልክልኝ
እግዚአብሔር የሰውዬውን ልብ ያራራልኝ::
ግን እነዚህን ሁለቱን ልጆቼን ባጣ ምን እሆናለሁ?
እንዳልኝ አምላክ ያውቃል::




ወንድማማቾቹም ሁሉን አዘጋጁ::
ገጸ በረከቶቹንም በከረጢቶች ውስጥ ከተቱ
በዛ ያለ ገንዘብም ይዘው ጉዞ ቀጠሉ::

ብንያምን ይዘው ግብፅ ሲደርሱ
ዮሴፍ ዘንድ ቀረቡ::
ዮሴፍም ብንያምን እንዳየ
ወንድማማቾቹ እልፍኝ እንዲገቡ አዘዘ::
እነርሱንም ለመጋበዝ ብሎ በሬ አሳረደ::
አገልጋዩም እንደታዘዘው አደረገ::
ወደ ዮሴፍ እልፍኝ አስገባቸው::
አገልጋዩም ውሃ አቀረበና
እግሮቻቸውን እንዲታጠቡ ነገራቸው::
ለአህዮቻቸውም ገለባ ሰጠ::
ስሞዖንንም ይዞት መጣና አገናኛቸው::

## የወንድማማቾቹ ስጋት

ወንድማማቾቹም ወደ እልፍኙ ሲገቡ
ደነገጡና እንዲህ ሲሉ ተነጋገሩ።
ዛሬ ጉድ ሊመጣብን ነው። ወደዚህ ያስገቡን
በዚያ ገንዘብ ምክንያት ይሆናል።
አይ ጉድ ባሪያዎች ሊያደርጉን ነው።
እንግዲህ አህዮቻችንንም ይወስዱብናል።
ባዶ እጃችንን መቅረታችን ነው ተባባሉ።





ኋላም ለዮሴፍ አገልጋይ እንዲህ አሉት።
ፊት እዚህ መጥተን እህል ገዝተን ነበር።
ወደ አገራችን ስንጓዝ መሸብን።
ስለዚህ መንገድ ለማደር ተገደድን።
ኋላም ለአህዮቻችን ጥሬ ልንሰጥ
ስልቻዎቻችንን ስንፈታ
በሁላችን ስልቻ ገንዘብ ተደርጎ አየን።
ባየንም ጊዜ በጣም ደንግጠን ነበር።
አሁን ገንዘቡን መልሰን አምጥተናልና
ይኸው ተቀበለን አሉት።
ቀጥለውም እኛ የሚቸግረን ነገር የለም።
ለሸመታ በቂ ገንዘብ ይዘን መጥተናል አሉ።

የቤቱም አገልጋይ መልሶ እንዲህ አለ።
ጨርሶ በምንም አትጨነቁ፣ አትፍሩ።
በስልቻዎቻችሁ ውስጥ
ገንዘብ አግኝተናል ብላችኋል።
አምላካችሁ አስቀምጦት ይሆናል።



በእኔ በኩል ገንዘብ ተቀብያችኋለሁ
መጨነቃችሁን ተውት አላቸው፡፡

## ከአገር ገዢው ጋር ግብዣ

ከዮሴፍ ጋር ምሣ በሚበሉበት ጊዜ
ያመጡዋቸውን ገጸ በረከቶች ሊሰጡ ተዘጋጁ፡፡
ከዚያም ዮሴፍ በመጣ ጊዜ
ገጸ በረከቶቻቸውን ይዘው ቀረቡ፡፡
    ዝቅ ብለው ሰላምታ በሰጡትም ጊዜ
    ደኅንነታቸውን ጠየቃቸው፡፡
    ከዚያም ሽማግሌ አባት አለን ብላችኋል
    እስካሁን በሕይወት አለ? ሲል ጠየቃቸው፡፡
    ጤናውስ እንዴት ነው? አላቸው፡፡
እነርሱም አባታችን በሕይወት አለ
ጤንነቱም መልካም ነው፡፡
አሉና ለጥ ብለው ሰገዱለት፡፡






ዮሴፍም ግራ ቀኙን እየተመለከተ
በተለይ ብንያምን እያየ
እንዲህ አላቸው፡፡
    ትንሽ ወንድም አለን ብላችሁ ነበር
    በጣቱም ወደ ልጁ እያመለከተ



ይህ እርሱ ነው? አለ።
ከዚያም ልጄ! እግዚአብሔር ይባርክህ አለው።
ዮሴፍ ወንድሙን ሲያይ እንባ ተናነቀው።
ወዲያው ወንድሞቹን ትቶ ወጥቶ
ወደ ክፍሉ ከገባ በኋላ አለቀሰ።

ከዚያም ፊቱን ታጥቦ መጣና
ተረጋግቶ አጠገባቸው ቁጭ አለ።
ከዚያም ግብዣው እንዲቀጥል አዘዘ።





ለእርሱ ምግብ ለብቻው ቀረበለት።
ወንድሞቹ ግን በአንድነት በሉ።
ወንድማማቾቹ በተራ እንደ እድሚያቸው ተቀመጡ።
ታላላቆቹ ከፊት ሆኑ።
ታናናሾቹ ቀጥለው ተቀመጡ።
በዕድሜ ተራ መቀመጣቸው ገረማቸው።
ዮሴፍም ፊት ለፊት ተቀመጠ።









ምግብ ከዮሴፍ ፊት ተላከላቸው::
ከዚያም ይጨመርላቸው ነበር::
ለብንያም ብዙ ተጨመረለት::
አምስት እጥፍ ተሰጠው::
ሁሉም ከዮሴፍ ጋር ስለበሉ ተደሰቱ::

## የዋንጫው ምሥጢር

ዮሴፍ ዋናውን አገልጋይ ጠራውና
እንዲህም ሲል አዘዘው::

የእነዚህን ሰዎች ስልቻዎች በእህል ሙላ::
የከፈሉትንም ገንዘብ ከላይ አኑር::
በታናሹ ልጅ ስልቻ ውስጥ ግን
የብር ዋንጫዬን አስቀምጥ::
ገንዘቡንም አብረህ አኑረው::


ዋናው አገልጋይም የተነገረውን አደረገ::
ወንድማማቾቹ በማለዳ አህዮቻቸውን ጫኑና
ወደ አገራቸው ተሸኙ::



ገና ከከተማው ሳይርቁ
ዮሴፍ አገልጋዩን ጠርቶ

ሰዎቹን በፍጥነት ተከተል::
ስትደርስባቸውም እንዲህ በላቸው::
እኛ ደስ የሚላችሁን አደረግንላችሁ::
በመልካም ፈንታ ክፉ ለምን አደረጋችሁ?
ጌታዬ ወደፊት የሚሆነውን ነገር
የሚያውቅበትን ዋንጫ ለምን ሰረቃችሁ?
ትልቅ ጥፋት ፈጽማችኋል በላቸው አለው::





## ለምን ይህን ጥፋት ፈጸማችሁ?

የአገልጋዮቹ አለቃም በፍጥነት ሄዶ ደረሰባቸውና
ዮሴፍ እንዳዘዘው ተናገራቸው::
እነርሱም ለምን ይህን ትጠይቀናለህ?
እኛ ይህን አላደረግንም አሉት::
ከፈለግህ ፈትሸን::
የተገኘበትን ሰው ልትገድለው ትችላለህ::
እኛም ባሪያዎችህ እንሆናለን አሉት::
አገልጋዩም ያላችሁት ጥሩ ነው
እንደተናገራችሁ አደርጋለሁ::
የተገኘበት ብቻ ባሪያዬ ይሆናል
ሌሎቻችሁ ግን ተመልሳችሁ
ወደ አገራችሁ ትሄዳላችሁ አላቸው::

## የብንያም ስልቻ

ኋላም ወንድማማቾቹ ስልቻዎቻቸውን ፈቱና
አገልጋዩም መፈተሽ ጀመረ
በመጀመሪያ የታላላቆቹን ስልቻዎች ፈተሸ::
ቀጥሎም ወደ ታናናሾቹ ስልቻዎች ተመለሰ
ይህን ጊዜ ዋንጫው በብንያም ስልቻ ውስጥ ተገኘ





ወንድማማቾቹም ይህን ጊዜ ደነገጡ::
ወዲያው በስልቻ ያለውን እህላቸውን ጭነው
ከአገልጋዩ ጋር ወደ ከተማ ተመለሱ::
ይሁዳና ሌሎቹም አብረው በመጡ ጊዜ
ወደ ዮሴፍ ዘንድ ቀረቡ::
ዮሴፍንም ፊት በነበረበት ሥፍራ አገኙት::
እንዳዩትም በእግሮቹ ሥር ተደፉ::
ዮሴፍም ለምን ይህን
አስነዋሪ ነገር አደረጋችሁ?



እንደ እኔ ያለ ታላቅ ሰው
ብዙ ምሥጢሮችን ያውቃል::
እናንተ ግን ይህን አታውቁም አላቸው::

ይሁዳም እንዲህ አለ::
ምንም ማለት አንችልም::
ምንም መልስ የለንም::
ተናግረን ከቶ ማስረዳትም ያቅተናል::
እግዚአብሔር ጥፋታችንን ገልጦብናል::
ዋንጫው በታናሻችን ዘንድ ስለተገኘ
ሁላችንም ባሪያዎችህ
ለመሆን ተዘጋጅተናል አለው::

ዮሴፍ ግን መልሶ አይደለም አይደለም!
ሁላችሁም ባሪያዎቼ አትሆኑም::
ባሪያዬ የሚሆነው ዋንጫውን የሰረቀው ብቻ ነው
እርሱ የእኔ ባሪያ ይሆናል::
የቀራችሁት ልትሄዱ ትችላላችሁ አላቸው::




## ብንያም ነፃ እንዲሆን የቀረበ አቤቱታ

ይህን ጊዜ ይሁዳ ለዮሴፍ እንዲህ አለ::
ጌታዬ ጥቂት እንድናገር ፍቀድልኝ::
እንደ ፈርዖን ታላቅ መሆንህን አውቃለሁ::
ቢሆንም ሳትቆጣ በትዕግሥት አድምጠኝ::

ባለፈው ጊዜ ጥያቄ በጠየከን ጊዜ
አባትም ወንድምም አላችሁ? አልከን::
እኛም ሽማግሌ አባት አለን አልንህ::
ትንሽ ወንድምም እንዳለን ነገርንህ::
የዚህ ልጅ ወንድም ሙቶአል
ሁለቱም የአንድ እናት ልጆች ናቸው::
አሁን የቀረው እርሱ ብቻ ነው::
አባታችንም በጣም ይወደዋል::
አንተ ደግሞ ወደ እኔ አምጡት አልከን::

እኛም ልጁ ከአባቱ ሊለይ አይችልም::
አባቱ ልጁ ከተለየው በሐዘን ይሞታል አልንህ::
አንተም መልሰህ እንድታመጡት
ካላመጣችሁ ፊቴን አታዩም አልከን::
ይህንንም ለአባታችን ነገርነው::
ኋላም ከእዚህ የወለድነው እህል አለቀ::
አባታችንም ሄዳችሁ ግዙ አለን::
እኛም ለአባታችን ልጁን ካላከህ እንጂ
ባዶ እጃችንን አንሄድም አልነው::





ስንሄድ ገዥው ፊት መቅረባችን አይቀርም::
ታዲያ ምን ይዘን ልንቀርብ ነው! አልነው::
አባታችንም መልሶ
ከሚቿዋ የምወዳት ሚስቴ ያገኘኋቸው
ሁለት ወንዶች ልጆች ናቸው::
ከሁለቱ አንዱ የለም::
እስከ ዛሬ ፈልጌ አላገኘሁትም::
የዱር አውሬ በልቶታል
ለዚህም እርግጠኛ ነኝ::
አሁን ደግሞ ይህኛውን እንውሰድ ትሉኛላችሁ::
አደጋ ቢደርስበት ምን እሆናለሁ?
አደጋ ከደረሰበት ደግሞ ኀዘኔ ይበረታል::
ኀዘኑም ይገድለኛል ብሏል አሉት::

## አባታችን ይሞትብናል

ይሁዳም ንግግሩን በመቀጠል
ስለዚህ ልጁን ይዤ መመለስ አለብኝ
አለበለዚያ አባቱ በኀዘን ይሞታል::
ልጁን በጣም አድርጎ ይወደዋል::



ይህን ልጅ ትተን መመለስ አንችልም::

ከተውነው አባታችን በብስጭት መሞቱ ነው::

እኔም ልጁን ልመልስ ቃል ገብቼ ነው የመጣሁት::

አባቴንም እንዲህ ብዬዋለሁ::

ብንያምን እንደወሰድሁት መልሼ አመጠዋለሁ

ባልመልሰው ግን ተጠያቂና በደለኛ ነኝ ብዬዋለሁ አለ::

ይሁዳም ቀጥሎ ጌታዬ እባክህን ስማኝ::

እኔ ባርያህ ልሁንልህ::

ልጁ ግን ወደ አባቱ ይመለስ::

ከወንድሞቹም ጋር ተመልሶ ይሂድ::

እኔ ልጁን ትቼ አልመለስም::

ልጁን ሳልይዝ የአባቴን ፊት ማየት አልፈልግም::

ልጁ ባይመለስ አባታችን በጣም ያዝናል::

ከሐዘኑ ብዛት ይሞትብናል::

ይህ ደግሞ ለእኔ ከባድ ነው አለ::



## <u>ዮሴፍ ምሥጢሩን ነገራቸው</u>

ዮሴፍ ይሁዳ የተናገረውን ካዳመጠ በኋላ

ዐይኖቹ እንባ አቀረሩ::

አገልጋዮቹ በአጠገቡ ቢኖሩም

ከቶ ሊታገስ አልቻለም::

አገልጋዮቹን ወደ እርሱ ጠራና

<u>ውጡ አላቸው</u>:: <u>አ</u>ገልጋዮቹም ወጡ::





ዮሴፍ በወንድሞቹ ፊት ከፍ ባለ ድምጽ አለቀሰ

እኔ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ አላቸው::

ቀጥሎም አባቴ በሕይወት አለ? ሲል ጠየቃቸው::

ወንድሞቹም ይህን ሲሰሙ ደነገጡ::

መናገርም አቃታቸው::

ዮሴፍ ሲያለቅስ ግብፃውያን በውጭ ነበሩ

ስለዚህ ፈርዖን የሆነውን ሲሰማ ቻለ::





## አስደናቂው የእግዚአብሔር ዓላማ

ዮሴፍም ወንድሞቹን በርኅራሄ ዐይን አያቸው::

ኑ ወዲህ ወደ እኔ ተጠጉ አላቸው::

ዮሴፍም እንዲህ አላቸው::

እኔ ለነጋዴዎች የሸጣችሁኝ ዮሴፍ ነኝ::

ነጋዴዎቹም ወደ ግብፅ አምጥተውኝ

ይኸው ትልቅ ሰው ሁኜአለሁ::

ስለዚህ ስለሸጣችሁኝ አትዘኑ::

ራሳችሁንም አትውቀሱ::

እኔ ወዲህ መምጣቴ ጠቅሞአል::

እንደምታዩት ብዙዎችን ከረሃብ አድኛለሁ::

ይህን ያደረገው እግዚአብሔር ነው አለ::

አሁን ረሃብ ከገባ ሁለት ዓመት ሆኖታል::

ገና አምስት የረሃብ ዓመት ይቀራል::

ምድሪቱ እህል ስለማታበቅል

የሚበላ እህል አይኖርም::

ስለዚህ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ

እኔን ወደ ግብፅ ላከኝ::

እናንተንም ከረሃብ ሊያድናችሁ ፈልጎ
ልጆቻችሁም እንዳይሞቱ ስለፈቀደ
ይኸውላችሁ እምላክ ወደዚህ አመጣኝ
አላቸው::

አምላክ ወደደኝና ከፍ አድርጎ
የፈርዖን ወዳጅ አደረገኝ::
በግብፅ ሁሉ ላይ ሾመኝ::
እንግዲህ ወደ አባቴ ሂዱና
እንዲህ ብላችሁ ንገሩት::
እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ
የግብፅ ገዥ አድርጎኛል::
እባክህን አባቴ ወደዚህ ናልኝ::
አንተና ልጆችህ፣ የልጅ ልጆችህ
በጎችህና ፍየሎችህ
ከብቶችህም ሁሉ ይምጡ::
ከእኔ ጋር ትኖራላችሁ::
የሚያስፈልግህንም አደርግልሃለሁ::
አምስት የረሃብ ዓመት ይቀራል::



ረሃብ ገና ይቆያል::
ስለዚህ ሁላችሁም መራብ የለባችሁም::
ከብቶችህም ሊጎዱ አይገባምና
ወዲህ ና ብሏል በሉት አላቸው::

ዮሴፍም ቀጥሎ እንዲህ አለ::
እኔ እነጋግሬአችኋለሁ::
ወንድማችሁ መሆኔን አውቃችኋል::
በሉ ወደ አባቴ ሂዱ::
ባለሥልጣን መሆኔን ንገሩት::
ባለጠጋ ሆኗል በሉት::
ያያችሁትን ሁሉ ንገሩት::
አባቴንም ቶሎ ይዛችሁልኝ ኑ አላቸው::

## ያማረ ፍጻሜ

ከዚያም ዮሴፍ እጆቹን ዘረጋን
በብንያም አንገት ላይ ተጠመጠመ::
ስቅስቅ ብሎም አለቀሰ

የቀሩትንም እየዞረ በተራ ሳመ
እነርሱም ስቅስቅ ብለው አለቀሱ።



ሁሉም በጣም ደስ አላቸው።
ፍርሃታቸውም ተወገደ።
ቤተሰብነት ተሰማቸው።



ዮሴፍንም በፍቅር ቀርበው
በወንድምነት ያነጋግሩት ጀመር።

## መጨረሻው ምን ሆነ?

ኋላም ፈርዖን ነገሩን ሰምቶ ስለነበር
በሁኔታው እጅግ ደስ አለው።
ከዚያም ዮሴፍን አስጠራና
ቶሎ ብለህ በከነዓን ያሉትን
አባትህንና ወንድሞችህን
ወደዚህ አስመጣ።
በጌሴም ተመችቷቸው
እንዲኖሩ አድርግ አለው።
የዮሴፍ ወንድሞችም ከተሰናበቱት በኋላ
መልእክቱን ሊነግሩ ወደ ከነዓን ተመለሱ።
ሲደርሱም አባታቸውን በደህና አገኙት።
እነርሱም ዮሴፍን በሕይወት እንዳለ
ትልቅ ሰው ሆኖ ተሹሞ እንዳገኙት
በነገሩት ጊዜ በጣም ደነገጠ።



በመጀመሪያ አላመነም ነበር::
ነገሩን ሲረዳ ደስታም ልቅሶም ተሰማው::
እነርሱም የተላኩትን በሙሉ በነገሩት ጊዜ
በሉ እግዚአብሔር ልጄን ለዚህ ካበቃው
እኔም ሄጄ በሕይወት መሆኑን አያለሁ::
እንግዲህ ሁሉን አዘጋጁ::
ቤተሰቦቻችሁም ይሰናዱ::
ዕቃዎቻችንንም በአህዮች ላይ ጫኑ::
የምትይዙትንም ሁሉ ያዙ::
እግዚአብሔር ፈቅዷልና እንሂድ አለ::
እነሱም ሁሉን ነገር አዘጋጅተው
በግብፅ ለመኖር ተነሱ::

ከከነዓን ተጉዘው ግብፅ ሲደርሱ
ዮሴፍ ብዙ ሰዎችን አስከትሎ
የሚሳፈሩባቸው ሰረገላዎችን አዘጋጅቶ
በሚያስደንቅ ሁኔታ ተቀበላቸው::
አባቱንም ባየ ጊዜ አንገቱ ላይ ተጠመጠመና
እያለቀሰ ስሞ ደህንነቱንም ጠየቀው::





ከዚያም ዮሴፍ አባቱንና ወንድሞቹን
ጥሩ ሥፍራ በሆነው በጌሴም
እንዲኖሩ ወደዚያ ይዟቸው ሄደ::
በዚያም የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ሰጣቸው::
ያዕቆብና ቤተሰቡ በሙሉ
በጌሴም ከብት እያረቡ
በደስታ ለብዙ ዓመታት ኖሩ::



